## ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 8 ኛ ሳምንት

# ዮሴፍ በግብፅ ሞገስን አገኘ

### ዓላማ

- የዮሴፍን ቀጣይ ታሪክ መማር፣ የመታመንን በረከትና መልስ ማጥናት የትምህርቱ መሠረታዊ ዓላማ ነው።

### ምንባብ

- ዘፍጥረት 39።

### መግቢያ

- ባለፈው ትምህርታችን የዮሴፍ ወንድሞች ያደረጉበት ክፉ ነገር ተምረናል። ታስታውሳላችሁ ምንና ለምን አደረጉት?
- ዛሬ ዮሴፍ በባርነት ከተሸጠ በኋላ ምን እንደገጠመው እንማራለን።

### የትምህርተ ይዘት፣

- የግብፅ ፈርኦን ሹም ዮሴፍን ከነጋዴዎቹ ገዛው ልጆች ፈርኦን ምን ማለት ነው? ሹምስ? ፈርኦን የግብፅ ነገስታት የንግስና መጠሪያ ሲሆን፣ ሹም ማለትም በንጉስ የሚሰጥ ስልጣንና ሹመት ነው።የሹሙም ስም ጲጥፋራ ነበር።
- ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት ሲሰራ እግዚአብሔር ሥራውን ሁሉ ይባርክለት ነበር። የሹሙም ቤት ተባረከ።ጲጥፋራ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑን ሲያውቅ ቤቱን እንዲያስተድር እንዲጠብቅለት፣ ሁሉንም ለዮሴፍ ተወለት።
- የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍ ክፉ ነገር እንዲሰራ ስትመክረው እርሱ ግን የእግዚአብሔር ሰው ስለነበር ኃጢአት አልሠራም አለ። በዚህም የጲጥፋራ ሚስት በሃሰት ወንጅላ ዮሴፍን አሳሰረችው።
- እግዚአብሔር ግን ዮሴፍ ታስሮም ከእርሱ ጋር ነበር። በእስር ቤቱ ጠባቂ ፊትም ሞገስ ሠጠው።
- የእስረኞች አለቃ አድርጐም ሾመው። እግዚአብሔር ያከናውንለት ነበር። ዮሴፍ በእስር ቤት ሆኖ ሕልም ይተረጉም ነበር፣
- ለአለቃውና በተለይም ደግሞ ለእግዚአብሔር ታማኝ ነበር።

### ጥያቄ፣

1. ዮሴፍን ወደ ግብፅ ያመጣው ማን ነበር?
2. ዮሴፍ ለምን ታሠረ?
3. ዮሴፍ በእስር ቤት እያለ ምን ተፈጠረ?
4. እግዘአብሔር ዮሴፍ በሄደበት ሁሉ ከእርሱ ጋር የሚሆነው ለምን ነበር?
5. እናንተስ ለቤተሰቦቻችሁ ለመምህሮቻችሁና ከሁሉም በላይ ደግሞ ለእግዚአብሔር ታማኝ ናችሁ?

### መዝሙር፣

እግዚአብሔር ይጠብቀን ከክፉ ፈተና፣
ዛሬም ቢሆን ነገም ቢሆን (2) ይጠብቀን ከክፉ ፈተና፣

ይቆየን።